# በመስከረም 20 ቀን 2014 ዓ.ም በተደረገው ምርጫ እና ህዝበ-ውሳኔ ላይ የተደረገ የምርጫ ትዝብት የመጀመሪያ ደረጃ ሪፖርት

መስከረም 22 ቀን 2014 ዓም

## *መግቢያ*

***የኢትዮጵያ የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች ሕብረት ለምርጫ*** በአገሪቱ የሚከናወኑ ምርጫዎች ነፃ እና ገለልተኛ እንዲሁም እንደ አካታችነት፣ ግልፅነት እና ተጠያቂነት የመሳሰሉትን አለም-አቀፍ መርሆዎችን መሰረት አድርገው መከናወናቸውን መታዘብ አንዱ ዓላማው አድርጎ መቋቋሙ ይታወቃል። ሕብረቱ ሰኔ 14 ቀን 2013 ዓ.ም የተደረገውን አገራዊ እና ክልላዊ ምርጫ 2050 ተቀማጭ፣ እንዲሁም ከ100 በላይ ተንቀሳቃሽ ታዛቢዎችን በማሰማራት ታዝቧል። ሰኔ 14 ቀን 2013 ዓ.ም በተካሄደው ምርጫ ሙሉ ለሙሉ ድምጽ ሊሰጥባቸው ባልቻለባቸው በሶማሌ እና በሀረሪ፣ እንዲሁም በአማራ፣ በኦሮሚያ እና በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልሎች አንዳንድ አካባቢዎች እና በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ህዝበ ውሳኔ መተላለፉን የኢትዮጵያ ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ በወቅቱ መግለጹ ይታወሳል። ምንም እንኳን የኢትዮጵያ ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ ምርጫ ባልተካሄደባቸው ቦታዎች ምርጫውን ጳጉሜ 1 ቀን 2013 ዓም እንደሚያካሂድ የገለፀ ቢሆንም፤ ነሃሴ 11 ቀን 2013 ዓም በሰጠው መግለጫ የድምጽ መስጫ ዕለቱ ወደ መስከረም 20 ቀን 2014 ዓ.ም መተላለፉን አሳውቋል። በዚሁ መግለጫም በሰኔ ወር ድምጽ ባልተሰጠባቸው አንዳንድ የአማራ፣ የቤኒሻንጉል ጉሙዝ እና የኦሮሚያ ክልል አካባቢዎች የድምጽ መስጠት ሂደቱ መስከረም 20 ቀን እንደማይከናወን ተገልጿል።

ሕብረቱ መስከረም 20 ቀን 2014 ዓ.ም በሀረሪ እና ሶማሌ ክልሎች የተደረጉ ምርጫዎች እንዲሁም በደቡብ ክልል ውስጥ በሚገኙ አንዳንድ ስፍራዎች የተደረገውን የህዝብ ተወካዮች ም/ቤት እና የክልል ም/ቤት ምርጫዎች እንዲሁም በዚሁ ክልል የተደረገውን የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ህዝበ ውሳኔ ታዝቧል። በተጨማሪም ለሀረሪ ብሄራዊ ጉባኤ መቀመጫዎች በአዲስ አበባ እና በድሬዳዋ ከተማ በተመሰረቱ የምርጫ ጣቢያዎች እንዲሁም በሶማሌ ክልል፣ ፋፈን ዞን ደንዳማ ወረዳ በሚገኘው የቆሎጂ የአገር ውስጥ ተፈናቃዮች ጊዜያዊ መጠለያ ውስጥ የተደረገውን የድምጽ አሰጣጥ ሂደት ታዝቧል።

ይህ የመስከረም 20 ቀን 2014 ዓ.ም ምርጫ የመጀመሪያ ደረጃ ሪፖርት ከላይ በተጠቀሱት የተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች ከተሰማሩ 956 ቋሚ እንዲሁም 37 ተንቀሳቃሽ የሕብረቱ ታዛቢዎች በተገኙ የትዝብት ሪፖርቶች ላይ የተመሰረተ ነው። ሕብረቱ በመደበኛ የድምጽ መስጫ ጣቢያዎች ካሰማራቸው ከ37 ተንቀሳቃሽ ታዛቢዎች መካከል ሰባቱን በልዩ ሁኔታ በማዘጋጀት በሰማሌ ፋፈን ዞን ደንዳማ ወረዳ ውስጥ በሚገኘው ቆሎጂ የአገር-ውስጥ ተፈናቃዮች መጠለያ ጣቢያ ውስጥ አሰማርቶ የምርጫ ሂደቱን ታዝቧል ይህ የምርጫ ትዝብት ሪፖርት ከሕብረቱ ታዛቢዎች በተሰበሰቡ 944 የምርጫ ቀን ሪፖርቶች እና 26 የአሳሳቢ ኹነት ሪፖርቶች ላይ የተመሰረተ ነው። ሕብረቱ ትኩረቱን በድምጽ መስጫ ጣቢያዎች አከፋፈት እና አደረጃጀት፣ እንዲሁም የድምጽ አሰጣጥ እና ቆጠራ ሂደት ላይ አድርጎ የምርጫ ትዝብቱን አከናውኗል።

በድምጽ- መስጫው ዕለት የሕብረቱ ታዛቢዎች በሳይንሳዊ ዘዴ የተዘጋጀ ትዝብት መጠይቅ (ቅፅ) የተሰጣቸው ሲሆን፤ በድምጽ መስጫው ዕለት በተለያዩ የድምጽ መስጫ ጣቢያዎች በመሰማራት ከድምጽ መስጫ ጣቢያዎች አከፋፈት እና አወቃቀር አንስቶ እስከ ድምጽ መስጠት እና ቆጠራ ድረስ ያሉትን ሁኔታዎች ታዝበዋል። በተጨማሪም አሳሳቢ ኹነቶች በሚያጋጥሙበት ወቅት በአፋጣኝ ለሕብረቱ ሪፖርት አድርገዋል። የሕብረቱ ቋሚ ታዛቢዎች በየተመደቡበት የድምጽ መስጫ ጣቢያዎች ከንጋቱ 11 ሰዓት ተኩል አንስቶ የድምጽ መስጠት ሂደቱ ተጀምሮ እስከሚጠናቀቅ ድረስ የታዘቡ ሲሆን፤ ከአንዳንድ ታዛቢዎቻችን በስተቀር አብዛኛዎቹ የድምጽ ቆጠራ ሂደቱን ታዝበዋል።

ሕብረቱ የኢትዮጵያ ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ ምርጫውን ባካሄደባቸው ቋንቋዎች ላይ ተመርኩዞ ባዘጋጀው መጠይቆች በመታገዝ በአጭር የፅሁፍ መልዕክት በበቂ ሁኔታ ከሰለጠኑ ታዛቢዎቹ ያሰባሰባቸውን መረጃዎች አጠናቅሯል። ከእነዚህ መጠይቆች በተጨማሪ የሕብረቱ ታዛቢዎች በድምጽ አሰጣጥ ወይም ቆጠራ ወቅት ያጋጠሙ እንዲሁም የምርጫውን ተዓማኒነት ጥያቄ ውስጥ የሚጥሉ ወይም የመራጮችን፣ የምርጫ አስፈፃሚዎችን፣ የእጩዎችን ወይም ሌሎች ከምርጫው ጋር ግንኙነት ያላቸውን አካላት ደህንነት አደጋ ላይ ሊጥሉ የሚችሉ "አሳሳቢ ኹነቶችን" አሰባስቧል። ከተዘዋዋሪ ታዛቢዎቹ እና በሀገር-ውስጥ ተፈናቃዮች ጊዜያዊ መጠለያ ውስጥ ካሰማራቸው ታዛቢዎቹ ጋር ተከታታይ የስልክ ልውውጦችን በማድረግ መረጃዎችን አሰባስቧል። ሕብረቱ በመረጃ ማዕከሉ ለማሰባሰብ፣ ለማጣራት እና ለማቀናበር እንዲሁም የምርጫ ትዝብት ሂደትን ለማሳለጥ የሚረዳ ዘመናዊ ቴክኖሎጂን ተጠቅሟል።

ይህ የሕብረቱ የመጀመሪያ ደረጃ የትዝብት ሪፖርት በድምጽ መስጫ ዕለት ሕብረቱ በሰጠው መግለጫ ላይ ይፋ የተደረጉትን ግኝቶች ያካትታል።

## የትዝብት ግኝቶች ማብራርያ

የሚከተለው የመጀመሪያ ደረጃ ግኝት ሕብረቱ ድምጽ በተሰጠባቸው ክልሎች ካሰማራቸው 956 ታዛቢዎች ባገኛቸው መረጃዎች ላይ በመመስረት የተጠናቀሩ ናቸው። በተጨማሪም በምርጫው ተዓማኒነት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ሊያሳድሩ የሚችሉ የአሳሳቢ ኹነት ሪፖርቶችን ካሰማራቸው ቋሚ እና ተንቀሳቃሽ ታዛቢዎች ሰብስቧል።

## በድምጽ መስጫ ጣቢያዎች በሰዓቱ መድረስን በተመለከተ

በድምጽ መስጫ ዕለት ከሚጠበቁ ወሳኝ ኹነቶች መካከል የምርጫ አስፈፃሚዎች በድምጽ መስጫ ጣቢያዎች በሰዓቱ መድረስ አንዱ ነው። የድምጽ አሰጣጥ ሂደቱን ከጠዋቱ 12 ሰዓት ለመጀመር እንዲያስችል፤ የምርጫ-አስፈፃሚዎች ቀድመው በድምጽ መስጫ ጣቢያዎች እንዲገኙ ይጠበቃል። በተመደቡበት የድምጽመስጫ ጣቢያ ከማለዳው 11 ሰዓት ጀምሮ በመድረስ ሪፖርቶቻቸውን ከላኩ የሕብረቱ 944 ታዛቢዎች መካከል 97 በመቶዎቹ የምርጫ አስፈፃሚዎች በድምጽ መስጫ ጣቢያዎች ቀድመው መገኘታቸውን አረጋግጠዋል።

98 በመቶ የሕብረቱ ታዛቢዎች የኢትዮጵያ ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ የሰጠውን የታዛቢነትን ማረጋገጫ ባጅችን በማሳየት ወደ ምርጫ ጣቢያ በመግባት እንዲታዘቡ ተፈቅዶላቸዋል። በዚህ ረገድ የኢትዮጵያ ብሄራዊ የምርጫ ቦርድ የታዛቢነት ባጅ ከሰኔ 14 ምርጫ በተሻለ ቅልጥፍና ለመስጠት መቻሉ በበጐ ጐኑ የሚታይ ነው። ይሁን እንጂ ሕብረቱ በድምፅ መስጫው ቀን ይፋ ባደረገው የምርጫ ዕለት የግማሽ ቀን ሪፖርት ላይ እንደገለፀው፣[1] በአንዳንድ የምርጫ አስፈፃሚዎች ዘንድ በሚታየው የመረጃ ክፍተት ጥቂት ታዛቢዎቻችን ወደ ድምፅ መስጫ ጣቢያ እንዳይገቡ እንቅፋት ፈጥሯል። ለምሳሌ በደቡብ ክልል ዳውሮ ልዩ ዞን፣ በሀረሪ ክልል በባቢሌ፤ በአዲስ አበባ የሀረሪ ብሄራዊ ጉባኤ የድምጽ መስጫ ጣቢያ የተመደቡ የተወሰኑ የሕብረቱ ታዛቢዎች በምርጫ አስፈፃሚዎች እንዳይታዘቡ ተከልክለዋል። ሕብረቱ ችግሩን ለኢትዮጵያ ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ በማሳወቅ በፍጥነት መፍትሔ እንዲያገኙ አድርጓል።

## የድምጽ መስጫ ጣቢያዎች አከፋፈት

በኢትዮጵያ የምርጫ ሕግ የድምጽ መስጫ ጣቢያዎች ድምጽ ለሚሰጡ መራጮች ከጠዋቱ 12 ሰዓት ጀምሮ ክፍት መሆን ይኖርባቸዋል። የመታዘብን አስፈላጊነት ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ሕብረቱ የድምጽ መስጫ ጣቢያዎች ለመራጮች ክፍት የሆኑበትን ሰዓት እንዲሁም የአከፋፈታቸውን ነባራዊ ሁኔታ የሚመለከቱ መረጃዎችን ሰብስቧል። በሕብረቱ ታዛቢዎች ሪፖርት መሰረት 98 በመቶ የሚሆኑት የድምጽ መስጫ ጣቢያዎች ከጠዋቱ 1 ሰዓት በፊት ለመራጮች ክፍት ሆነው ነበር። 99 በመቶ የሚሆትኑ የሕብረቱ ታዛቢዎች በድምጽ መስጫው ቀን የኢትዮጵያ የምርጫ ሕግ መሰረት በድምጽ መስጫ ጣቢያዎች 200 ሜትር ርቀት ውስጥ የምረጡኝ ቅስቀሳዎች በምርጫ ቀን እንዳልተካሄዱ እንዲሁም እንዲሁም የምርጫ ቅስቀሳ ቁሳቁስ እንዳልታዩ ታዝቧል።

---

[1] የኢትዮጵያ ሲቪል ማህበራት ሕብረት ለምርጫ ድረ-ገጽ https://www.cecoe.org/

## የድምጽ መስጫ ጣቢያዎች አደረጃጀት

በምርጫ ሂደት ውስጥ ወሳኝ ከሆኑ ቁልፍ ተግባራት መካከል የድምጽ መስጫ ጣቢያዎች አደረጃጀት አንዱ ነው። ሕብረቱ የድምጽ መስጫ ጣቢያዎቹን መታዘቡ የምርጫ ሂደቱን ቅቡልነት ለመገምገም እንዲያስችለው ብቻ ሳይሆን የኮቪድ-19 ቫይረስ ስርጭትን ለመከላከል ከተደረገ ጥረት አንፃር የቦርዱን ዝግጅት ለመታዘብ አስችሎታል። ከዚህ በታች የድምጽ መስጫ ጣቢያዎች አደረጃጀት የተመለከቱት ዝርዝር ግኝቶች ቀርበዋል፤

- መራጮች በቀላሉ ድምጻቸውን ለመስጠት እንዲችሉ የድምጽ መስጫ ጣቢያዎች ለሁሉም በቀላሉ ተደራሽ በሆኑ አካባቢዎች ሊቋቋሙ ይገባል። በሕብረቱ ታዛቢዎች ሪፖርት መሰረት 96 በመቶ የድምጽ መስጫ ጣቢያዎች ለአካል-ጉዳተኞች እና የመንቀሳቀስ ችግር ላለባቸው መራጮች (በእድሜ ለገፉ፣ ለነፍሰጡሮች እና ህፃናትን ለያዙ) ምቹ በሆኑ ቦታዎች ላይ ተቋቁመዋል።
- በተመሳሳይ 97 በመቶ የድምጽ መስጫ ጣቢያዎች ለሴቶችም ሆነ ለወንዶች በእኩል መጠን ተደራሽ ነበሩ። ይህ ግኝት በድምጽ መስጫ ጣቢያዎች ተደራሽነት ረገድ በሰኔ ወር ከተካሄደው ምርጫ ከነበረው የ87 በመቶ ግኝት አንፃር የተሻለ መሆኑ ታይቷል፤
- የኢትዮጵያ ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ መመሪያ የድምጽ አሰጣጥ ሂደቱን ለማስጀመር ቢያንስ 3 የምርጫ አስፈፃሚዎች መገኘት እንዳለባቸው ይደነግጋል። ሕብረቱ በታዘበባቸው የድምጽ መስጫ ጣቢያዎች በአማካይ 4 የምርጫ አስፈፃሚዎች ተገኝተዋል። ከምርጫ አስፈፃሚዎቹም መካከል 37 በመቶዎቹ ሴቶች የነበሩ ሲሆን፣ 23 በመቶዎቹ የምርጫ ጣቢያ ኃላፊዎች ነበሩ። ምንም እንኳን ይህ ቁጥር አበረታች ቢሆንም ቦርዱ በእያንዳንዱ የድምጽ መስጫ ጣቢያ ቢያንስ አንዲት ሴት የምርጫ አስፈፃሚ እንድትኖር ለማድረግ እንደሚጥር ከገለፀው አንፃር ሲታይ ዝቅተኛ ነው። በተጨማሪም  ሕብረቱ ከታዘባቸው የድምጽ መስጫ ጣቢያዎች በ11 በመቶዎቹ ሴት የምርጫ አስፈፃሚዎች አለመኖራቸው ተስተውሏል፤
- የድምጽ መስጫ ጣቢያ ቁሳቁስ አቅርቦት መሟላት ለድምጽ አሰጣጥ ሂደት እጅግ ወሳኝ ነው። ከድምጽ መስጫ ዕለት አስቀድሞ ሁሉም መራጮች ድምጽ መስጠት እንዲችሉ የምርጫ ቁሳቁስ በእያንዳንዱ የድምጽ መስጫ ጣቢያ ማሟላቱን ቦርዱ ማረጋገጥ ይጠበቅበታል። በ99 በመቶ የሕብረቱ ታዛቢዎች ሪፖርት መሰረት ወሳኝ የምርጫ ቁሳቁስ ማለትም የድምጽ መስጫ ወረቀት፣ የድምጽ መስጫ ሳጥን፣ የድምጽ መስጫ ሳጥን ማሸጊያ፣ የቦርዱ ህጋዊ ማህተም፣ የማይለቅ የጣት ቀለም፣ የማመሳከሪያ ወረቀት ተሟልተው እንደነበር ገልፀዋል። በሰኔ 2013 ዓ.ም ምርጫ ከታዩ ተግዳሮቶች መካከል የድምጽ መስጫ ጣቢያ ቁሳቁስ እጥረት እና የቁሳቁስ አድራሻ መቀያየር አንዱ እንደነበር ይታወሳል።[2] በአንፃሩ መስከረም 20 ቀን በተካሄደው ምርጫ ቦርዱ የምርጫ ቁሳቁስን በበቂ ሁኔታ ማድረስ መቻሉ ታይቷል።
- ከሕብረቱ የትዝብት ግኝቶች መካከል ሌላው የድምጽ መስጫ ጣቢያዎች ሲከፈቱ የተገኙ የፓርቲ ተወካዮችን ይመለከታል። የሕብረቱ ታዛቢዎች ከታዘቧቸው የድምጽ መስጫ ጣቢያዎች ውስጥ 77 በመቶ በሚሆኑት የፓርቲ ተወካዮች ተገኝተዋል። ይህ የፓርቲ ተወካዮች በድምጽ መስጫ ጣቢያዎች መገኘት ህዝበ-ውሳኔ ብቻ በተከናወነባቸው ጣቢያዎች ወደ 40 በመቶ ዝቅ ይላል፤
- የኮሮና ቫይረስ ወረርሺኝ በሕብረቱ ልዩ ትኩረት ከተደረገባቸው ጉዳዮች መካከል አንዱ ነው። ሕብረቱ የኮቪድ 19 ቫይረስን ለመከላከል ከድምጽ መስጫ ጣቢያዎች አደረጃጀት ጋር በተያያዘ የተወሰዱ የጥንቃቄ እርምጃዎችን ታዝቧል። በድምጽ መስጫ ጣቢያዎች ከውስጥም ሆነ ከውጭ ያላቸው አደረጃጀት አካላዊ መራራቅን አክብሮ ድምጽ ለመስጠት የሚያስችሉ መሆናቸውን ገምግሟል። በታዛቢዎች ሪፖርት መሰረት 89 በመቶ የድምጽ መስጫ ጣቢያዎች አደረጃጀት መራጮች አካላዊ ርቀትን ጠብቀው ድምጽ ለመስጠት ያስቻሉ ነበሩ። የድምጽ መስጫ ጣቢያዎች ውስጣዊ አደረጃጀትም 96 በመቶዎቹ አካላዊ መራራቅን ለመጠበቅ የሚያስችሉ እንደነበሩ ታይቷል።

## የድምጽ አሰጣጥ ሂደት

የድምጽ-መስጫ ጣቢያዎች ከተከፈቱ እና ከተደራጁ በኋላ ቀጣዩ የድምጽ አሰጣጥ ሂደቱ ነው። በመስከረም 20 ቀን 2014 ዓ.ም አብዛኛዎቹ የድምጽ መስጫ ጣቢያዎች የተከፈቱት ከላይ እንደተገለጸው ከጠዋቱ 1 ሰዓት ሲሆን ፤ በሶማሌ ክልል እንዲሁም በደቡብ ክልል የክልል ምክር ቤቶች እና የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ምርጫ በተካሄደባቸው አካባቢዎች የድምጽ መስጫ ጣቢያዎች እስከ ምሽቱ 12 ሰዓት ድረስ ክፍት ነበሩ። ከምሽቱ 12 ሰዓት ላይ በነበረው ረጅም ሰልፍ የድምጽ መስጠት ሂደቱ እስከ ምሽቱ 2 ሰዓት ድረስ በሐረር ክልል እና የሕዝበ-ውሳኔ በተደረገባቸው የደቡብ ክልል አካባቢዎች እንዲራዘም ተደርጓል። የሕብረቱ ታዛቢዎች ድምጽ መስጠት በተደነገገው ሰዓት በተጠናቀቀባቸው እንዲሁም ሰዓቱ ካለፈ በኋላ በተጠናቀቀባቸው ቦታዎች  የድምጽ አሰጣጥ ሂደቱን በመታዘብ በድምጽ መስጫ ጣቢያዎች ውስጥ ሙሉ ቀን ቆይተዋል። በዚህም መሰረት ሕብረቱ በድምጽ መስጠት ሂደት ላይ ከታዛቢዎቹ የሰበሰባቸውን ግኝቶች እንደሚከተለው ቀርበዋል፦

---

[2] የኢትዮጵያ ሲቪል ማህበራት ድርጅቶች ሕብረት ለምርጫ (CECOE), የድምጽ መስጫ ጣቢያዎች የድምጽ መስጠት መጀመርን የተመለከተ ጋዜጣዊ መግለጫ [https://www.cecoe.org/wp-content/uploads/2021/06/Election-2021-Preliminary-findings-EN.pdf] (23 June 2021)

- ከኢትዮጵያ ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ ፍቃድ የተሰጣቸው ታዛቢዎች የድምጽ መስጫ ጣቢያዎች ውስጥ የመግባት መብት ያላቸው ሲሆን ታዛቢዎች የድምጽ መስጫ ጣቢያዎችን እንዲለቁ ሊጠየቁ የሚችሉት ከኮሮና ቫይረስ ወረርሺኝ ጋር ግንኙነት ባለው ምክንያት ብቻ ነው። ይህም ቢሆን ጊዜያዊ የሆነ እንጂ ታዛቢዎችን ሙሉ በሙሉ የድምጽ መስጫ ሂደቱን እንዳይታዘቡ የሚከለክል አይደለም። ከዚህ መመሪያ ጋር በተያያዘ 98 በመቶ በሚሆኑ ኢጋጣሚዎች የሕብረቱ ታዛቢዎች በድምጽ መስጫው ቀን በማንኛውም ሰዓት ከድምጽ መስጫ ጣቢያ እንዲወጡ አልተደረጉም። ሆኖም ግን በ23 ኢጋጣሚዎች የሕብረቱ ታዛቢዎች ከኮቪድ-19 ጋር በተያያዘ ምክንያት የምርጫ ጣቢያውን በጊዜያዊነት ለቀው እንዲወጡ መደረጋቸውን ገልጸዋል። ይህን በሰኔ ወር ከተካሄደው ምርጫ ሪፖርት ላይ በተገኘው መረጃ መሰረት ከኮቪድ-19 ጋር ግንኙነት በሌለው ምክንያት የድምጽ መስጫ ጣቢያዎችን እንዲለቁ ከተጠየቁበት 12 ኢጋጣሚዎች ጋር ሲነጻጸር በመስከረም 20 በተካሄደው ምርጫ ተመሳሳይ ሪፖርቶች አለመኖራቸውን መገንዘብ ይቻላል።

- ሁሉም የህብረተሰቡ ክፍሎች በምርጫ ሂደት ውስጥ እንዲሳተፉ ለማስቻል ድምፅ ለመስጠት የሌሎችን ድጋፍ የሚሹ መራጮች ቅድሚያ እንዲያገኙ እና ህጉ በሚፈቅደው መሰረት በመረጡት ሰው ድጋፍ እንዲያገኙ ተፈቅዷል። 98 በመቶ በሚሆኑት ሕብረቱ በታዘበባቸው የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች አካል-ጉዳተኞች እና የመንቀሳቀስ ችግር ያለባቸው መራጮች ቅድሚያ እንዲያገኙ የተደረጉ ሲሆን፤ 96 በመቶዎቹ በመረጡት ሰው ድጋፍ አግኝተዋል። በሌላ በኩል ሕብረቱ በታዘባቸው 9 በመቶ የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች ነፍሰ ጡር መራጮች እንዲሁም ማንበብና መፃፍ የማይችሉ መራጮች ድጋፍ አግኝተዋል።

- ከትዝብት ሂደቱ ግኝቶች ጋር በተያያዘ፤ 20 በመቶ በሚሆኑት የሕብረቱ ታዛቢዎች በተገኙባቸው የድምጽ መስጫ ጣቢያዎች ቢያንስ አንድ መራጭ በማይለቅ ቀለም ምልክት ሳይደረግበት እንዲመርጥ ተደርጓል። ሕብረቱ ከታዘባቸው የድምጽ መስጫ ጣቢያዎች ውስጥ 95 በመቶ በሚሆኑት የድምጽ መስጫ ወረቀቶች ለመራጮች ከመታደላቸው አስቀድሞ ሕጋዊ ማህተም ሲደረግባቸው፤ 5 በመቶ በሚሆኑት ደግሞ የድምጽ መስጫ ወረቀቶቹ ለመራጮች ከመታደላቸው በፊት አንዳንድ ጊዜ በሃላፊዎች ማህተም ሲደረግባቸው በሌላ ጊዜ ደግሞ ማህተም ሳይደረግባቸው ለመራጮች መሰጠታቸውን ያመላክታል። በሰኔ ወር በተካሄደው ምርጫ ሕብረቱ ከታዘባቸው የድምጽ መስጫ ጣቢያዎች ውስጥ 9 በመቶ በሚሆኑ የድምጽ መስጫ ወረቀቶች ላይ ሕጋዊ ማህተም አለማድረግ እንደነበር ይታወሳል። በአንፃሩ በመስከረም 20 በተደረገው ምርጫ 3 በመቶ የሚሆኑ የድምጽ መስጫ ወረቀቶች ብቻ ማህተም ሳይደረግባቸው ለመራጮች መሰጠታቸው አዎንታዊ ለውጥ እንዳሳየ ያመለክታል።

- 90 በመቶ በሚሆኑት ሕብረቱ በታዘባቸው የምርጫ ጣቢያዎች የድምጽ አሰጣጥ ሂደቱ ምስጥራዊነት እንደተጠበቀ አመላክተዋል። 99 በመቶ የሚሆኑ ሕብረቱ ያሰማራቸው ታዛቢዎች የድምጽ መስጫ ሳጥኖች ድምጽ ሲሰጥባቸው በነበሩበት ሰዓታት በሙሉ በድምጽ መስጫ ጣቢያዎች ውስጥ በግልጽ ሊታይ በሚችል ቦታ መቀመጣቸውን ሪፖርት አድርገዋል።

- በድምጽ መስጫ ቀን በመራጮች መዝገብ ላይ ስማቸው የተገኙ መራጮች መምረጥ የሚችሉት ለመራጭነት በተመዘገቡበት ጣቢያ ብቻ ነው። ስለሆነም የምርጫ አስፈፃሚዎች በመራጮች መዝገብ ላይ ያልተመዘገበ ማንኛውንም ሰው እንዳይመርጥ እንዲሁም የተመዘገቡ ደግሞ እንዲመርጡ የመፍቀድ ኃላፊነት አለባቸው። የሕብረቱ ታዛቢዎች 9 በመቶ በሚሆኑ ትዝብት በተደረገባቸው ድምጽ መስጫ ጣቢያዎች ቢያንስ አንድ መራጭ የመራጮች መዝገብ ላይ ስሙ ሳይኖር ድምጽ እንዲሰጥ ተደርጓል። በተያያዘም 34 በመቶ በሚሆኑት ትዝብት በተደረገባቸው የድምጽ መስጫ ጣቢያዎች ቢያንስ አንድ መራጭ የመራጮች መዝገብ ላይ ስሙ እያለ እንዳይመርጥ ተከልክሏል። ይህ ሁኔታ የዜጎችን የፖለቲካ መብቶች የሚጋፋ ከመሆኑ አንፃር አሳሳቢ ነው። በተጨማሪም ይህ ክስተት 19 በመቶ በሚሆኑ የሕዝበ-ውሳኔ ምርጫ በተካሄደባቸው ቦታዎች መስተዋሉ ችግሩ የሕዝበ-ውሳኔ ምርጫ በተካሄደባቸው አካባቢዎች በዝቅተኛ ደረጃ ላይ መኖሩን አመላካች ነው።

- በኢትዮጵያ ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ መመሪያ መሰረት የድምጽ መስጫ ጊዜ ከምሽቱ 12 ሰዓት ላይ ያበቃል። የድምጽ መስጫ ጣቢያዎች ሁሉም መራጮች ድምጻቸውን እንዲሰጡ ለማስቻል እስከ ምሽቱ 12 ሰዓት ድረስ ለመራጮች ክፍት መሆን አለባቸው። 85 በመቶ በሚሆኑት የሕብረቱ ታዛቢዎች በድምጽ መስጫ ቀን የታዘቧቸው ጣቢያዎች ከምሽቱ 12 ሰዓት እስከ 1 ሰዓት መካከል ባለው ጊዜ የተዘጉ ሲሆን 15 በመቶ የሚሆኑት የድምጽ መስጫ ጣቢያዎች ከምሽቱ 1 ሰዓት እስከ 3 ሰዓት ባለው ጊዜ መዘጋታቸው ታውቋል። ከድምጽ መስጫ ጣቢያዎች መዝጊያ ሰአት ጋር በተገናኘ ሌላኛው መሟላት ያለበት አስፈላጊ ስነ-ስርዓት ከምሽቱ 12 ሰዓት ላይ በድምጽ መስጫ ጣቢያዎች ድምጽ ለመስጠት የተሰለፉ መራጮች ካሉ ድምጻቸውን እንዲሰጡ ማድረግ ነው። 52 በመቶ በሚሆኑት ሕብረቱ በታዘባቸው የድምጽ መስጫ ጣቢያዎች መራጮች ከምሽቱ 12 ሰዓት ላይ በሰልፍ ላይ ያልነበሩ ሲሆን፤ 47 በመቶ በሚሆኑት የትዝብት ሪፖርቶች

ደግሞ ከምሽቱ 12 ሰዓት ላይ በድምጽ መስጫ ጣቢያዎች ድምጻቸውን ለመስጠት የተሰለፉ መራጮች ድምጻቸውን እንዲሰጡ መደረጉን ያመለክታሉ።

- የኮቪድ-19 ወረርሺኝን በተመለከተ 72 በመቶ በሚሆኑት ሕብረቱ በታዘባቸው የድምጽ መስጫ ጣቢያዎች የምርጫ አስፈፃሚዎች የአፍ እና አፍንጫ መሸፈኛዎችን በድምጽ አሰጣጡ ሂደት ላይ ሙሉ በሙሉ ያደረጉ ሲሆን 27 በመቶ የሚሆኑት መራጮች ደግሞ በከፊል የአፍ እና አፍንጫ መሸፈኛ ማድረጋቸው ሪፖርት ተደርጓል። በተመሳሳይ ሁኔታ ሕብረቱ መራጮች የአፍ እና አፍንጫ መሸፈኛ ማድረግ ወይም አለማድረጋቸውን የታዘበ ሲሆን ትዝብት በተደረገባቸው 34 በመቶ  በሚሆኑት የድምጽ መስጫ ጣቢያዎች ውስጥ ድምጻቸውን ከሰጡ መራጮች መካከል በሁሉም ሰዓት የአፍ እና አፍንጫ መሸፈኛ አድርገዋም። 55 በመቶ የሚሆኑት ደግሞ በከፊል የአፍ እና አፍንጫ መሸፈኛ እንዳደረጉ እንዲሁም 12 በመቶ የሚሆኑት ሙሉ በሙሉ የአፍ እና አፍንጫ መሸፈኛ እንዳላደረጉ ሕብረቱ ተገንዝቧል። ቁጥሩ የሚያሳየው በድምጽ መስጫ ጣቢያዎች ውስጥ ያለውን የኮቪድ-19  ቅድመ-መከላከል መመሪያዎች በከፍተኛ ደረጃ አለመከበሩ ሲሆን ይህም ሕብረቱን ያሳስበዋል። በመጨረሻም፣ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የአፍ እና አፍንጫ መሸፈኛ አለማድረግ መራጮችን ድምጽ እንዳይሰጡ መከልከያ ምክንያት አለመሆኑን መግለጹ ይታወሳል። በእነዚህ ሁኔታዎች መራጮች አፍ እና አፍንጫቸውን በማንኛውም አይነት ጨርቅ መሸፈን ከቻሉ ድምጻቸውን መስጠት ይችላሉ። ሆኖም ሕብረቱ ከሰበሰባቸው ሪፖርቶች 7 በመቶ በሚሆኑት ምርጫ ጣቢያዎች ለመምረጥ የሄዱ መራጮች ምንም እንኳን መደበኛ ከሆነው የአፍ እና አፍንጫ መሸፈኛ (mask) ውጭ ያሉ የጨርቅ መሸፈኛዎችን (Face covering) ቢያደርጉም የአፍ እና የአፍንጫ መሸፈኛ (mask) ባለማድረጋቸው ድምጻቸውን እንዳይሰጡ ተደርገዋል። ሕብረቱ የዚህን ጉዳይ አሳሳቢነት ተገንዝቧል።

## የድምጽ ቆጠራ ሂደት

በድምጽ መስጫ ሂደት ውስጥ የድምጽቆጠራ የመጨረሻው ሂደት ነው። ከድምጽ መስጫ ጣቢያዎች መዘጋት በኋላ የምርጫ አስፈፃሚዎች ሁሉም የድምጽ መስጫ ወረቀቶች መቆጠራቸውን እንዲሁም በሕግ የተቀመጡ ሁኔታዎች ካልተሟሉ ደግሞ የድምጽ ቆጠራው በድምጽ መስጫ ጣቢያዎች ውስጥ አለመከናወኑን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለባቸው።

- ተቀባይነት ካለው ታዛቢዎችን ከኮቪድ-19 ጋር በተያያዙ ምክንያቶች የድምጽ መስጫ ጣቢያውን በጊዜያዊነት እንዲለቁ ከማድረግ በስተቀር በድምጽ መስጠት ሂደቱ ታዛቢዎች የድምጽ ቆጠራውን ሂደት እንዲታዘቡ ተፈቅዷል። ወደ 19 የሚደርሱ ታዛቢዎች(2 በመቶ የሚሆኑት ማለት ነው) ከኮቪድ-19 ጋር በተገናኘ ምክንያት የድምጽ መስጫ ጣቢያዎችን እንዲለቁ የተደረገ ቢሆንም 98 በመቶ የሚሆኑ ታዛቢዎች በድምጽ መስጫ ጣቢያዎች ውስጥ ቆይተው የድምጽ ቆጠራ ሂደቱን ለመታዘብ እና ሪፖርት ለማቅረብ ችለዋል።

- 99 በመቶ የሕብረቱ ታዛቢዎች በተገኙባቸው የድምጽ መስጫ ጣቢያዎች የድምፅ ቆጠራ በዕለቱ ተካሂዶ ነበር። 99 በመቶ የሚሆኑት የሕብረቱ ታዛቢዎች የድምጽ ቆጠራ ከተጀመረ በኋላ ሂደቱ እንዳልተቋረጠ፤ ጣልቃ ገብነት፣ ማስፈራራት ወይም ትንኮሳ  በድምጽ ቆጠራ ወቅት አለመኖሩን ሪፖርት አድርገዋል። በአንድ አጋጣሚ የድምጽ ቆጠራ ሂደቱ  የድምጽ መስጫ ጣቢያ ኃላፊዋ በድምጽ ቆጠራ ሂደት ወቅት ባጋጠማት ከፍተኛ የጤና እክል ቆጠራው ለአንድ ሰዓት ያህል የተቋረጠ ሲሆን በሌላ አጋጣሚ ደግሞ በከባድ ዝናብ አማካኝነት የድምጽ ቆጠራ ሂደቱ ተቋርጦ ነበር።የኢትዮጵያ ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ ሴቶች፣ አካል-ጉዳተኞች እና ነፍሰ-ጡር ሴቶች የምርጫ አስፈፃሚዎች በሆኑባቸው የድምጽ መስጫ ጣቢያዎች ውስጥ የድምጽ ቆጠራው እንዲቋረጥ እና በነጋታው እንዲካሄድ ግልጽ መመሪያ ሰጥቷል። አንድ የሕብረቱ ታዛቢ ተገኝቶ በነበረበት የድምጽ መስጫ ጣቢያ የምትገኝ ሴት የምርጫ አስፈፃሚ የቦርዱን መመሪያ በመከተል ቃለ-ጉባኤ በመያዝ የድምጽ ቆጠራ ሂደቱን ወደሚቀጥለው ቀን ለማስተላለፍ ያደረገችውን ጥረት በማስተጓጎል ለፓርቲ ወኪሎች ከተሰጠው የውክልና ሚና ውጪ ማንም ግለሰብ ከድምጽ መስጫ ጣቢያው እንዳይወጣ ከልክሏል።

- የሕብረቱ ታዛቢዎች በድምጽ መስጫ ቀን በተገኙባቸው የድምጽ መስጫ ጣቢያዎች በአማካይ ሶስት የፓርቲ ወኪሎች ተገኝተው ነበር።

- የሕብረቱ ትዝብት ሪፖርት እንደሚያሳየው በድምጽ መስጫ ጣቢያዎች በአማካይ አንድ ቅሬታ እንደቀረበ ያመላክታል። ይህም በሰኔው ምርጫ ከተጎበኙ እያንዳንዱ የድምጽ መስጫ ጣቢያዎች ውስጥ ስድስት ቅሬታ መኖር ጋር ሲነፃፀር ከፍተኛ መቀነስ እንዳለ ለመረዳት ይቻላል። ከቅሬታዎች ጋር በተገናኘ ሕብረቱ ከታዛቢዎች ጋር ባደረጋቸው የስልክ ውይይቶች ብዛት ባላቸው የድምጽ መስጫ ጣቢያዎች ቅሬታዎችን በድምጽ መስጫ ጣቢያ ደረጃ የሚፈቱ የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎች ቢቋቋሙም በተወሰኑ የምርጫ ጣቢያዎች ግን በድምጽ መስጫ ጣቢያዎች ውስጥ የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎች እንዳልተቋቋሙ ሕብረቱ ለመረዳት ችሏል።

- ከድምጽ ቆጠራ ሂደት ጋር የተገናኙ ግኝቶች እንደሚያሳዩት የሕብረቱ ታዛቢዎች 97 በመቶ በሚሆኑ ትዝብት በተደረገባቸው የድምጽ መስጫ ጣቢያዎች የምርጫ አስፈፃሚዎች ዋጋ ያላቸው የድምጽ መስጫ ወረቀቶችን ለመለየት ወጥነት ያላቸውን መመዘኛዎች ተጠቅመዋል። በተጨማሪም 97 በመቶ የሚሆኑት የትዝብት ሪፖርቶች መራጮች በድምጽ መስጫ ወረቀቶች ላይ ያኖሯቸው ምልክቶች በድምጽ መስጫ ቀን በተደረገው የድምጽ ቆጠራ ሂደት ላይ የምርጫ አስፈጻሚዎች በግልጽ እንዳሳዩ እና ቆጠራ እንዳከናወኑ ያመላክታል። በመጨረሻም የሕብረቱ ታዛቢዎች የውጤት እና የማመሳከርያ ቅጽ 98 በመቶ በሚሆኑ የድምጽ መስጫ ጣቢያዎች ውጭ መለጠፋቸውን መታዘባቸውን ገልጸዋል። ይህም በሰኔው ምርጫ የዚህ ቅጽ መለጠፍን በተመለከተ ከነበረው የ73 በመቶ ውጤት አኳያ ሲታይ ከፍተኛ መሻሻል መታየቱን ይመሰክራል።

## በምርጫ ቀን ስለተፈጠሩ አሳሳቢ ኹነቶች

ሕብረቱ የድምጽ አሰጣጥ እና ቆጠራ ሂደትን ምርጫ በተካሄደባቸው እና ታዛቢዎቹን ባሰማራባቸው የምርጫ ጣቢያዎች ከመታዘብ በተጨማሪ፤ የተለያዩ የአሳሳቢ ኹነት ሪፖርቶችን ተቀብሏል። ታዛቢዎች ልዩ ትኩረት ሰጥተው ከተከታተሏቸው ጉዳዮች መካከል የታዛቢዎች እንዳይታዘቡ መከልከል፣ የድምጽ መስጫ ጣቢያዎች በህግ በተከለከሉ ስፍራዎች መገኘት፣ የድምጽ መስጫ ቁሳቁስ እጥረት ወይም መጓደል፣ የድምጽ መስጠት ወይም ቆጠራ ሂደት መቋረጥ እንዲሁም ሌሎች የምርጫ ሰነ- ስርዓት መጓደል እና ከፀጥታ ጋር የተገናኙ ችግሮች ይጠቀሳሉ።

በሰኔ ወር በተካሄደው ምርጫ ሕብረቱ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸውን የአሳሳቢ ኹነት ሪፖርቶችን በድምጽ መስጠት እና ቆጠራ ሂደቱ ላይ ተቀብሎ ነበር። በመስከረም 20 ቀን 2014 ዓ.ም በተደረገው ምርጫ 67 አሳሳቢ ኹነቶችን ከታዛቢዎች ተቀብሎ በመረጃ ማዕከሉ በኩል ተገቢውን ማጣራት በማድረግ 26 አሳሳቢ ኹነቶች መከሰታቸውን አረጋግጧል። ካለፈው የሰኔ ወር ምርጫ ጋር ሲነጻጸር የአሳሳቢ ኹነት ሪፖርት ቁጥሮች ቀንሰዋል። ታዛቢዎቻችን የሚከተሉትን ዋና ዋና አሳሳቢ ሁነቶችን ሪፖርት አድርገዋል።

- ወደ ድምጽ መስጫ ጣቢያዎች ውስጥ እንዳይገቡ መከልከል የሕብረቱ ታዛቢዎች ካጋጠሟቸው አሳሳቢ ኹነቶች መካከል ዋነኛው ነው። በደቡብ ክልል በከፋ እና ዳውሮ ዞን፣ በሀረሪ ክልል፣ በሶማሌ ክልል በፋፈን ዞን እንዲሁም በአዲስ አበባ ለሀረሪ ብሔራዊ ጉባኤ ድምፅ በሚሰጥበት አንድ የምርጫ ጣቢያ የተሰማሩ ጥቂት የሕብረቱ ታዛቢዎች የታዛቢነት ባጃቸውን ቢያሳዩም እንዳይታዘቡ ተከልክለዋል። በተለይም በደቡብ ክልል በዳውሮ ዞን ውስጥ የተሰማራ አንድ የሕብረቱ ታዛቢ በፖሊስ ከንጋቱ 11 ሰዓት ተኩል እስከ ረፋዱ አምስት ሰዓት ድረስ ታስሯል። ምንም እንኳን ሁሉም የተጠቀሱት ክልከላዎች እና የሕብረቱ አንድ ታዛቢን መታሰር በፍጥነት ለቦርዱ በማድረስ ችግሮቹ እንዲፈቱ ለማድረግ ቢቻልም፤ በአንዳንድ የመንግስት አካላት እና የምርጫ አስፈፃሚዎች ላይ የሚታየው ታዛቢዎችን እንዳይታዘቡ መከልከል ሊታረም የሚገባው ነው።
- ሌላው በሕብረቱ ታዛቢዎች በኩል ሲደርስ የነበረው የአሳሳቢ ሁነት በተደጋጋሚ ድምጽ መስጠት ነው፡፡ የሕብረቱ ታዛቢዎች ይህንን ክስተት በተለይ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል ወላይታ ዞን ውስጥ በሶስት የተለያዩ አጋጣሚዎች በተደጋጋሚ ሲፈጸም ታዝበዋል። የመጀመሪያው የትዝብት ሪፖርትም አምስት ግለሰቦች በተደጋጋሚ ጊዜያት በአማካይ እያንዳንዳቸው እስከ 20 ጊዜ ድምጽ ሲሰጡ መዋላቸውን ከትዝብት ሪፖርታችን ለመረዳት ተችሏል። በዚሁ ክልል በተመሳሳይ ሁኔታ ሶስት ግለሰቦች እያንዳንዳቸው ከሁለት እስከ ሶስት ጊዜያት በአንድ የድምጽ መስጫ ጣቢያ መምረጣቸው እና በተመሳሳይ አንድ ግለሰብ በተደጋጋሚ ጊዜ ድምጽ ሲሰጥ መታዘባቸውን የሕብረቱ ታዛቢዎች አመልክተዋል።
- የድምጽ መስጠት ሂደቱ ከምሽቱ 12 ሰዓት ላይ እንደሚጠናቀቅ እና የምርጫ ጣቢያዎች ለቆጠራ እንደሚዘጉ ቢታወቅም የድምጽ መስጫ ጣቢያዎች መዝጊያ ወቅት ላይ ለመምረጥ በሰልፍ ላይ የነበሩ መራጮችን ማስተናገድ ሲገባ ከዚህ በተለየ መልኩ በሶማሌ ክልል 20 ደምጽ ለመስጠት በሰልፍ ላይ ከምሽቱ 12 ሰዓት በፊት የነበሩ መራጮች ቢኖሩም ከሕግ ውጪ ድምጽ እንዳይሰጡ ተከልክለዋል። ሕብረቱ የዜጎችን ድምጽ መስጠት መከልከልን አሳሳቢነት በመረዳት ለምርጫ አስፈጻሚ አካላት በሚሰጡ ስልጠናዎች ወቅት ትኩረት እንዲደረግባቸው እና መሰል አሰራሮች ዳግመኛ እንዳይፈጸሙ በጽኑ ያሳስባል።
- ሌላው ሕብረቱ በጅግጅጋ ከተማ ተሰማርተው ከነበሩ ታዛቢዎቹ የደረሰዉ የአሳሳቢ ኹነት ሪፖርት ከድምጽ አሰጣጥ ሚስጥራዊነት አለመጠበቅ ጋር የተያያዘ ነበር። በቦታው የተሰማራ አንድ ታዛቢ እንደገለጸልን ታዛቢው ይታዘብበት በነበረው የድምጽ መስጫ ጣቢያ ውስጥ በሚገኘው ሚስጥራዊ መሆን ባለበት የድምጽ ምልክት ማድረጊያ ክፍል ውስጥ አንዲት ግለሰብ ቀኑን ሙሉ መገኘቷ ተገልጿል።

ከዚህ በተጨማሪ  የድምጽ መስጫ ሳጥኖች ለመራጮች፣ ለምርጫ አስፈጻሚዎች እና ለታዛቢዎች ግልጽ በሆኑ ቦታዎች ላይ በዚሁ የድምጽ መስጫ አለመቀመጡ ተገልጿል።

እነዚህ እና ሌሎች  በድምጽ መስጫው ዕለት ለሕብረቱ የደረሱ የአሳሳቢ ኹነት ሪፖርቶች ምንም እንኳን በተናጠል የተከሰቱ ባይሆንም የድምጽ አሰጣጥ ሂደቱ ላይ የተስተዋሉ ቁልፍ ተግዳሮቶች ናቸው። ሕብረቱ የኢትዮጵያ ብሄራዊ ምርጫ ቦርድን ማስተካከያ ይሻሉ ብሎ ባመነባቸው ጉዳዮች ለቦርዱ ሪፖርት አድርጓል።

## የአገር-ውስጥ ተፈናቃዮች ድምጽ አሰጣጥ

የኢትዮጵያ ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ ከመስከረም 20 ቀን 2014 ዓ.ም. ምርጫ ጋር በተያያዘ ካሳለፋቸው ውሳኔዎች መካከል ሰፊ ቁጥር ያላቸው የአገር-ውስጥ ተፈናቃዮች በሚገኙበት በቆሎጂ የተፈናቃዮች መጠለያ ውስጥ የሚገኙ ተፈናቃዮች በምርጫ እንዲሳተፉ ያሳለፈው ውሳኔ አበረታች ነው። ሕብረቱ በ2008 ዓ.ም. መጨረሻ በተቋቋመው እና በሶማሌ ክልል፣ ፋፈን ዞን ደንደማ ወረዳ በሚገኘው የቆሎጂ የአገር-ውስጥ ተፈናቃዮች መጠለያ ውስጥ የተደረገውን የድምጽ አሰጣጥ ሁኔታ ታዝቧል። የአገር ውስጥ ተፈናቃዮችን በምርጫ ውስጥ የመሳተፍ አስፈላጊነት በመረዳት፤ ሕብረቱ 7 ተንቀሳቃሽ የምርጫ ታዛቢዎችን እና በልዩ ሁኔታ የሰለጠኑ አጥኚዎችን አሰማርቶ በመጠለያ ጣቢያው የተካሄዱ የድምጽ አሰጣጥ እና ቆጠራ ሂደቶችን እንዲገመግሙ አሰማርቷል። በቆሎጂ  የሀገር-ውስጥ ተፈናቃዮች ጊዜያዊ መጠለያ ውስጥ ከሚገኙት የድምጽ መስጫ ጣቢያዎች ውስጥ በ23ቱ በመደበኛ የትዝብት መጠይቅ እና በልዩ ሁኔታ በተዘጋጁ የአገር-ውስጥ ተፈናቃዮች የምርጫ ተሳትፎ መጠይቅ መሰረት ትዝብቱን አከናውኗል።

በኢትዮጵያ ብሄራዊ የምርጫ ቦርድ መመሪያ መሠረት የአገር-ውስጥ ተፈናቃዮች ምርጫ በልዩ የድምጽ አሰጣጥ ፈርጅ ከሚካተቱት ውስጥ አንዱ ነው። በቆሎጂ መጠለያ ጣቢያ ውስጥ በተሰማሩት 7 የሕብረቱ ታዛቢዎች ሪፖርት መሰረት ሁሉም (41) የድምጽ መስጫ ጣቢያዎች በሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች ጊዜያዊ መጠለያ ጣቢያ ውስጥ የተቋቋሙ ናቸው። ታዛቢዎቻችን ትዝብታቸውን ባደረጉባቸው የድምጽ መስጫ ጣቢያዎች ከመጠለያ ጣቢያ ውጪ የመጡ መራጮች ድምጽ ሲሰጡ አልተመለከቱም። የሕብረቱ ታዛቢዎች ከመራጮች በሰበሰቡት መረጃ  መሰረት የኢትዮጵያ ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ የመራጮች ምዝገባ ያካሄደው የተፈናቃይነት መታወቂያን መሰረት በማድረግ ነበር። የሕብረቱ ታዛቢዎች የድምጽ መስጠት ሂደት ከመጀመሩ በፊት ወደ መጠለያ ጣቢያው በመድረስ እየተዘዋወሩ የድምጽ መስጫ ጣቢያዎችን የጐበኙ ሲሆን፤ በታዘባቸው የምርጫ ጣቢያዎች የድምጽ መስጠት ሂደቱ የተጀመረው ከጠዋቱ 1 ሰዓት በኋላ ነበር።

በቆሎጂ የአገር-ውስጥ ተፈናቃዮች መጠለያ ጣቢያ የተካሄደው ምርጫ ሁሉን አካታች እንዲሁም ማንኛውም ሰው ከምርጫ መገለል የለበትም የሚለውን መርህ ከማረጋገጥ አንጻር አንድ እርምጃ ወደፊት የተራመደ መሆኑን አመልካች ነው። ሕብረቱ የኢትዮጵያ ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ እና የአገር-ውስጥ ተፈናቃዮች በሚኖሩባቸው ጣቢያዎች ሃላፊዎች በመጠለያ ጣቢያው ውስጥ የሚኖሩ ተፈናቃዮች ድምጽ እንዲሰጡ የወሰዱትን ተነሳሽነት እና ያደረጉትን ጥረት ያደንቃል። ሆኖም  የሕብረቱ ታዛቢዎች የተወሰኑ የሥነ-ስርዓት መዛነፎች እና ሌሎች ተግዳሮቶች በድምጽ አሰጣጥ ሂደቱ መከሰታቸውን መታዘብ ችለዋል። ከስነ-ሥርዓት አኳያ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮችን የመሳሰሉ ማህበረሰቦች (ለምሳሌ፡- የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች፤ በወታደር ካምፖች ውስጥ የሚኖሩ ወታደሮች) ደምጻቸውን ለመጡበት አከባበቢ እንዲሰጡ ይደረጋል። ነገር ግን በቆሎጂ ካምፕ በተደረገው የድምጽ-አሰጣጥ ተፈናቃዮች ድምጻቸውን በተጠለሉበት አካባቢ እጩ ተወዳዳሪ እንዲሰጡ ተደርጓል። ሕብረቱ ከታዘባቸው ተግዳሮቶች አንዱ አብዛኛዎቹ መራጮች በድምጽ መስጫ ወረቀት ላይ እንዴት ምልክት እንደሚያደርጉ አለማወቃቸው ወይም ማንበብና መፃፍ ባለመቻላቸው አንዳንድ ጠቃሚ የሆኑ የአመራረጥ ስርዓቶችን ተከትለው መምረጥ አለመቻላቸው ነበር። በዚህም ምክንያት አብዛኞቹ መራጮች የሌሎች ሰዎች ድጋፍ አስፈልጓቸዋል። በመጨረሻም የሕብረቱ ታዛቢዎች የታዘቡት ሌላ ተግዳሮት በምርጫ አስፈፃሚዎች የማስፈፀም አቅም ውስንነት የተነሳ የፓርቲ ወኪሎች በአንዳንድ ምርጫ የማስፈፀም ሂደት ውስጥ (የድምጽ መስጫ ወረቀትን ማደል) ሲሳተፉ ተመልክተዋል። የሕብረቱ ታዛቢዎችም በሁለት የምርጫ ጣቢያዎች በምርጫ አስፈፃሚዎቹ *"የምርጫ ማስፈፀም ሥራውን አግዙን"* የሚል ጥያቄ ቀርቦላቸው አልተቀበሉም።

## መደምደሚያ

የኢትዮጵያ የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች ሕብረት ለምርጫ የኢትዮጵያ ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ መስከረም 20 ቀን 2014 ዓ.ም ያካሄደውን ምርጫ ለመታዘብ 956 ቋሚ እንዲሁም 37 ተንቀሳቃሽ ታዛቢዎች ያሰማራ ሲሆን ከእነዚህም መካከል 7 ተንቀሳቃሽ ታዛቢዎችን የአገር-ውስጥ ተፈናቃዮችን የድምፅ አሰጣጥ እና ቆጠራ ሂደት እንዲታዘቡ አድርጓል። በዚህም መሰረት ከዚህ በታች የተመለከቱትን በጎ ጎኖች እና ሊሻሻሉ የሚገቡ ነጥቦችን መታዘብ ችሏል።

መስከረም 20 ቀን 2014 ዓ.ም የተካሄደው ምርጫ በሰኔ 14 ቀን 2013 ዓ.ም ከተካሄደው የድምፅ መስጠት ሂደት አንፃር ከዚህ በታች በተዘረዘሩት ነጥቦች ላይ የተሻለ እንደነበር ሕብረቱ ታዝቧል።

1. የኢትዮጵያ ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ ምርጫውን ለማካሄድ ያደረገው ቅድመ-ዝግጅት በተለይም በቂ የድምፅ መስጫ ቁሳቁስ አቅርቦትን ከሚሟላት አንፃር እንዲሁም ለምርጫ ታዛቢዎች ቀደም ብሎ የታዛቢነት ባጅ መስጠት መቻሉ፤
2. የአገር-ውስጥ ተፈናቃዬች በድምፅ መስጠት ሂደቱ ውስጥ እንዲሳተፉ በማድረግ የፖለቲካ ተሳትፎ መብታቸውን በተለይም የመምረጥ መብታቸውን እንዲጠቀሙ ለማስቻል መሞከሩ፤
3. ምርጫ በተካሄደባቸው በአብዛኛው አካባቢዎች ምርጫው በተያዘለት ሰዓት ተጀምሮ መጠናቀቁ መልካም የሚባል ሲሆን ተጨማሪ የድምፅ መስጫ ሰዓት ባስፈለገባቸው የሀረሪ ክልል ምርጫ እና የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልልነት ህዝበ ውሳኔ ተጨማሪ 2 ሰዓታት በመስጠት ዜጐችን የመምረጥ መብቶቻቸውን እንዲጠቀሙ ማስቻሉ፤
4. የሕብረቱ ታዛቢዎች የምርጫ ትዝብታቸውን በሚያከናውኑበት ወቅት ያጋጥሚቸው እና ለቦርዱ በወቅቱ የቀረቡ ችግሮችን በፍጥነት በመፍታት ከሕብረቱ ጋር በትብብር መንፈስ መስራት መቻሉ፤ በዋነኛነት የሚጠቀሱ ናቸው።

በአንፃሩ ከላይ የተጠቀሱት በጎ ጎኖች እንደተጠበቁ ሆነው የኢትዮጵያ ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ ትኩረት ሊያደርግባቸው የሚገቡ ክፍተቶችም ታይተዋል።

1. ሕብረቱ በታዘባቸው አንዳንድ የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች ላይ የምርጫ አስፈፃሚዎች አቅም ማነስ ታይቷል። ይህም ታዛቢዎችን መከልከልን እንዲሁም በምርጫ ማስፈፀሙ ሥራ ላይም በሁለት አጋጣሚዎች የሕብረቱ ታዛቢዎች ሙያዊ ትብብር እንዲያደርጉ መጠየቃቸው፤
2. ሕብረቱ በታዘባቸው አንዳንድ የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች ላይ የምርጫ አስፈፃሚዎች በኢትዮጵያ ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ ፍቃድ የተሰጣቸው ሕብረቱ ያሰማራቸውን ታዛቢዎች መከልከላቸው ብሎም እስከማሰር የደረሱባቸው አጋጣሚዎች መኖራቸው፤
3. በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል በወላይታ ዞን፣ በሶዶ ከተማ አንድ የመራጮች መዝገብ ጠፍቷል፤ እንዲሁም በዚሁ ክልል አንዳንድ መራጮች በተደጋጋሚ ድምፅ ሲሰጡ ታይተዋል። የኢትዮጵያ ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ በእነዚህ ጉዳዮች ላይ ተጨማሪ ምርመራ እንዲያደርግ ህብረቱ ይጠይቃል፤
4. በጅግጂጋ ከተማ ከተሰማራ አንድ ታዛቢ በደረሰን መረጃ መሰረት በአንድ የድምፅ-መስጫ ጣቢያ ውስጥ አንዲት ግለሰብ አግባብ ባልሆነ መልኩ በሚስጥር የድምፅ ምልክት ማድረጊያ ክፍል ውስጥ ቀኑን ሙሉ የነበረች ሲሆን የድምፅ-መስጫ ሳጥኑም ለመራጮች፣ ለታዛቢዎች እና ለምርጫ-አስፈፃሚዎች በግልፅ በሚታይ ቦታ አለመቀመጡ ተስተውሏል፤
5. ምንም እንኳን ሕብረቱ ለምርጫ ትዝብት ባደረገው ቅድመ-ዝግጅት ወቅት ከቦርዱ ከፍተኛ የስራ ትብብር የተደረገለት ቢሆንም በአንዳንድ አጋጣሚዎች (ለምሳሌ፡ ሕብረቱ የአገር-ውስጥ ተፈናቃዮች ምርጫ የሚደረግባቸውን መጠለያዎች የሚገኙበትን ስፍራ እና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮች) ግን አስፈላጊ መረጃዎችን ለማግኘት አልቻለም፤
6. ሕብረቱ በተፈናቃዮች መጠለያ ባደረገው ትዝብት በመጠለያው ውስጥ የሚገኙ መራጮች ድምፃቸውን ለመስጠት ገደብ የሚያደርጉ የአቅም ውስንነቶችን ታዝቧል። በመሆኑም እነዚህን ክፍተቶች ለመሙላት የመራጮችን አቅም ለማጎልበት ሁሉም የሚመለከታቸው አካላት በጋራ እንዲሰሩ ህብረቱ በፅኑ ያምናል።

ከላይ ከተጠቀሱ ቦርዱ ሊያሻሽላቸው ከሚገቡ ጉዳዬች በተጨማሪ በሕብረቱ ትኩረት ያገኙ አንዳንድ ጉዳዮችም አሉ። በድምፅ መስጫ ጣቢያዎች የፖለቲካ ፓርቲዎች ተወካዬች ብዛት ዝቅተኛ መሆኑን አስተውለናል። ይህም የፓለቲካ ፓርቲዎች በመስከረም 20 በተካሄደው ምርጫ ያደረጉት ተሳትፎ አነስተኛ መሆኑን መገንዘብ ተችሏል።

የኢትዮጵያ የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች ሕብረት ለምርጫ በድምፅ መስጫ ዕለት ከታዛቢዎቹ ከሰበሰባቸው መረጃዎች በተጨማሪ በቅድመ-ምርጫ ከምርጫው ጋር የተያያዙ ጉዳዮች ላይ ያሰባሰባቸውን እና በድህረ-ምርጫ ወቅት ያለውን አጠቃላይ ሁኔታ የሚያገኛቸውን መረጃዎች ማጣራቱን ይቀጥላል። በተጨማሪም መስከረም 20 ቀን 2014 ዓም የተካሄደውን ምርጫ ትዝብት ግኝቱን ከሰኔ 2013 የምርጫ ትዝብት ግኝቶቹ ጋር በማዋሃድ ሙሉ የምርጫ ትዝብት ሪፖርቱን ከምክረ ኃሳብ ጋር ይፋ የሚያደርግ መሆኑን ይገልፃል።

**የኢትዮጵያ የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች ሕብረት ለምርጫ**
**አዲስ አበባ**
**መስከረም 22 ቀን 2014 ዓም**